የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እና 16

1. “እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩት ድረስ እዚህ ካሉት ውስጥ ሞትን የማይቀምሱ አሉ።” ተብሎ የተነገረለት ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ለ) ጴጥሮስ ሐ) እስጢፋኖስ መ) ያዕቆብ

2. "ይህ ሕዝብ በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ ልባቸው ግን ከእኔ እጅግ ይርቃሉ።" ብሎ የተናገረው ነቢይ ማን ነው?
ሀ) ኤርምያስ ለ) ኢሳይያስ ሐ) ሆሴዕ መ) ኤልሳዕ

3. ጌታ በከነዓናዊቷ ሴት ምን ተመለከተ?
ሀ) ትሕትና ለ) ጥበብ ሐ) ሃይማኖት መ) ሁሉም

4. "ዕውሮችን የሚመሩ ዕውሮች ናቸውና " የተባሉት እነማን ናቸው?
ሀ) ሐዋርያት ለ) ምዕመናን ሐ) ፈሪሳውያን መ) ሀ እና ሐ

5. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ባርኮ አብዝቶ የመገባቸው?
ሀ) አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ
ለ) ሰባት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ
ሐ) ሰባት እንጀራ እና ጥቂት ዓሳ
መ) ምንም ስላልያዙ ሊመግባቸው አልቻለም

6. ጌታ "ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ " ሲል
ሀ) እንጀራ እንዳልያዙ ለማጠየቅ ነው
ለ) ሰዱቃውያን በማይኖሩበት እንዲኖሩ ሲነግራቸው ነው
ሐ) ከሰዱቃውያን ትምህርት እንዲጠበቁ ሲያሳስባቸው ነው
መ) ሁሉም

7. "አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ " ብሎ የመለሰው ሐዋርያ ማን ነበር?
ሀ) የዮና ልጅ ስምዖን
ለ) ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ
ሐ) ጴጥሮስ
መ) ሀ እና ሐ

8. ጌታችን ጴጥሮስን "አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ሂድ፤ እንቅፋት ሆነህብኛል " ያለው ለምንድን ነው?
ሀ) ጌታ አይሙት ማለት ነቢያትን ሐሰተኞች ማድረግ ስለሚሆን ነው
ለ) በጴጥሮስ አንጻር ሰይጣንን ሲገሥጽ ነው
ሐ) ጴጥሮስን ከሐዋርያት ለይቶ ሲያወግዝ ነው
መ) ሀ እና ለ

9. ጌታ ለጴጥሮስ ከሰጠው ቃልኪዳን ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ
ለ) በምድር የፈታው በሰማይ እንዲፈታ፤ በምድር ያሰረው በሰማይም እንዲታሰር
ሐ) በምድር አንድ ያደረገው በሰማይም አንድ እንዲሆን
መ) መልሱ የለም

10."የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?" ብሎ ጌታ በጠየቃቸው ጊዜ ከመለሱለት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ለ) ኤርምያስ ሐ) ኤልያስ መ) መጥምቁ ዮሐንስ

11. ሰዎች ጌታን መጥምቁ ዮሐንስ ነው የሚሉት ለምን ነበር?
ሀ) በበረሃ ስለሚኖር
ለ) ማር እና አንበጣ ብቻ እየበላ ስለሚኖር
ሐ) ንጽሕናውን አይተው
መ) ሁሉም

12. ጌታ 7 እንጀራና ጥቂት ዓሳ አብዝቶ፣ ባርኮ ያበላቸው ሰዎች ቁጥር ስንት ነበር?
ሀ) ከሴቶች እና ከሕጻናት በቀር 5000
ለ) ከሴቶች እና ከሕጻናት በቀር 4000
ሐ) ከሴቶች እና ከሕጻናት ጋር 4000
መ) መልሱ የለም

13. ከሚከተሉት ውስት ሐሰት የሆነው የቱ ነው?
ሀ) በአፍ የሚገባ ሳይሆን ከአፍ የሚወጣ ሰውን ያረክሳል
ለ) ከአፍ የሚወጣ ሁሉ ከልብ አይወጣም
ሐ) ከአፍ የሚወጣ ከልብ ላይሆን ስለሚችል ሰውን አይጎዳውም
መ) ለ እና ሐ

14. ከከነዓናዊቷ ሴት ታሪክ ምን እንገነዘባለን?
ሀ) ጌታ በዘር ለሚመሳሰሉት ብቻ እንጂ ለሌሎች ተዐምራትን አያደርግም
ለ) ጌታ በትሕትና እና በ ሃይማኖት ለጠየቁት ጆሮውን ያዘነብላል
ሐ) ወንጌል የተሰበከው ለተወሰኑ ነገዶች ተመርጦ ነው
መ) ሀ እና ሐ

15. "ይህ ህዝብ በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው ግን ከእኔ እጅግ ይርቃሉ" ሲል
ሀ) ዕሩቅ ብእሲ ይሉኛል
ለ) አምላክነቴን ይክዳሉ
ሐ) ምንም ቢሉ ልባቸው ንጹሕ ነው
መ) ሀ እና ለ

16. “ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡— አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ፡ አለ።”
ይህንን ምስክርነት ለጴጥሮስ የገለጠለት ማን ነው?
ሀ) ስጋ እና ደሙ ለ) ዓለማዊ እወቀቱ ሐ)እግዚአብሔር መ)ሁሉም

17. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን መከተል የሚፈልግ ቢኖር ምን ያድርግ አለ?
ሀ) እንዳሻው እየበላ እየጠጣ ይኑር
ለ) ራሱን ይካድ
ሐ) መስቀሉን ይሸከም
መ) ለ እና ሐ

18. "ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው፡ አላቸው።"
ይህንን ሲል ጌታችን ምን ማለቱ ነው?
ሀ) ጾም እንደማያስፈልግ ሲናገር
ለ) ከልባችን ክፉ ሐሳብ በአፋችን የምንናገረው ነው ሚያረክሰን
ሐ) እዳሪ ያረክሳል
መ) ሁሉም

19. አንተ ዓለት ነህ የተባለው ማን ነው?
ሀ) ስምኦን ለ) አስቆሮቱ ይሁዳ ሐ) ናትናኤል መ) ዮሐንስ

20. “አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም፡ ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።" እንዲህ ብሎ ጌታችንን የለመነው ማን ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ዮሐንስ ሐ) ይሁዳ መ) ማቴዎስ